# የምድረበዳው ማድጋ

## The Urn in the Wilderness

በሱዛን ከሚንግስ
እ.ኤ.አ አፕሪል 20፥2005 ዓ.ም [ባሃሳ ማሌዢያ]

by *Susan Cummings*
April 20, 2005 [Bahasa Malaysia]

ብዙም አትክልት ያልነበረበት ነገር ግን ብዙ ድንጋዮችና ወጣ ገባ መልክአምድር ያለውን ሰፊ መሬትን ተመለከትሁ፥ጥቂት በብዛት የበቀሉ ትናንሽ ቁጥቋጦዎች አንዳንድ ነገሮች ያሉበት። በረሃ አልነበረም፥ነገር ግን ምድረበዳማ ቦታ። በዚህ ስፍራ የተበታተኑ የሸክላ ስብርባሪዎች ወይም ተበታትነውና ተራርቀው የተቀመጡ እቃዎች ነበሩ።

ንፋስ በስብርባሪዎቹ ላይ መንፈስ ጀመረና ስብርባሪዎቹን ወደ ላይ ያነሣቸው ጀመር፥እናም ምንም እንኳን እያንዳንዱ ስባሪ የራሱ የሆነ ገጽታ ቢኖረውም እርስ በእርሳቸው መገናኘትና አንዱ የአንዱ የሆነ ይመስል መገጣጠም ጀመሩ። የሆነ ማድጋ ዓይነት ነገር መሥራት ጀመሩ። ግዙፍ የሆነ ማድጋ ሆነና በምድሩ ላይ ተቀመጠ እናም የተለያዩ ቀለማት የነበሩት ሲሆን የተሠራውም መሬት ላይ ወዳድቀው ከነበሩት የተለያዩ ዓይነት ስብርባሪዎች ነው፥ እንደዛም ሆኖ፥ ሁሉም ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ሁኔታ ተገጣጥመዋል፥ ከመጀመሪያውኑ ከአንድ አካል የነበሩ ይመስል።

ከዚያም ጌታ አጠገቤ ቆመና እንዲህ አለኝ፥

“*በፊትሽ የምታዪው የተቃረበውን ቅሬታዎቼን የማጠራበትን ወቅት (Season of Refining) ነው። እቃዎቼን ሰባብሬ በታተንኳቸው እናም በሙላት ወደ እሳቱ አመጣኋቸውና እያንዳንደን መለያቸውን ከእነርሱ አስወገድሁት፥ምክንያቱ ደግሞ ከእነርሱ የቀደመ ማንነት ምንም ነገር እኔ በዚህ አዲስ ወቅት ለእነርሱ ባለኝ አዲስ እቅድ ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ ነው። እኔን የሚቃወመው ነገር ሁሉ ከእነርሱ ተወግዷል፥እናም አመድ ሆኖ ተሰባብሯል፥በትንፋሼም ተወግዷል፥ከእነርሱ ውስጥም የሥጋን (ሥጋዊነት) ምልክት ሁሉ አስወጥቷል፥ በውስጥም (በሥጋ ውስጥ) ተገድበው የነበሩ ልቦችን አስለቅቋል፥ እናም እንዲለቀቁና እንደገና መምታት እንዲጀምሩ አድርጓቸዋል።*”

“*ምድረበዳው አሁን ያለፈ ወቅት ነው። ቅሬታዎቼ ወደ ቦታቸው ከፍ እያሉና ማንነታቸውን፥በእኔ ያላቸውን ዓላማ ወደ መረዳት እየመጡ ነው። በብቸኝነትና በመካንነት ከእኔ ጋር በተጓዙባቸው ጊዜዎች አስተምሬአቸዋለው በእጄም መግቤአቸዋለሁ። ፍቅሬንም ብርታቴን አይተዋል። ፍርዴን አጥብቀው ይይዛሉ እናም አሁን በምድር ክበብ ሁሉ በሚነደው በፍትሕ ሰዓት ይቆማሉ።*”

“*ቆሞ ያየሽው ማድጋ በምድር ላይ የሚፈሱት ቅሬታዎቼ ናቸው። በምድር ላይ ፈቃዴን ሳከናውን፥ በውስጣቸው የምኖርባቸውና የምለቀቅባቸው (የምገለጥባቸው) እቃዎች ናቸው። ሕዝቤን በራሴ (በእኔ) እየሞላሁ ነው። ይህን ለአንቺ አሳይቼሻለሁ። አንቺ የሆነ ድርሻ ትሸከሚያለሽ፥ልክ እነርሱ እንደሚሸከሙትና እንደሆኑት። በብዙ መንገድ ከሕዝቤ ውስጥ ወደ ፊት (ወደ ግልጥ) እመጣለሁ፥ እንደመረጥሁት ወደ ፊት እመጣለሁ፥ሥራዬንም እሠራለሁ፥እናም ዓለም ወይም ቤተክርስቲያን እንደምትፈልገው ወይም እንደምትሻው አይሆንም፥ወይም እንደሚገምቱት እንኳን፥እኔ ብቻ አምላክ ነኝና፥ሰውም አይደለሁም። ሰው ከእኔ ጋር አንድ*

*እስካልሆነ ድረስ ሊያውቀኝ አይችልም። የእኔ መንገድ የሰው መንገድ አይደለም አልያም እንደ ቤተክርስቲያን መንገድም አይደለም።"*

"*ቃሌ የእኔ በሆኑትና የእኔ ባልሆኑት መካከል ልዩነትን ያመጣል። መሰባበሩ ተጀምሯል እናም መለያየቱ በኃይል መቀጠል ጀምሯል፥ በመካከል ያለውም ልዩነቱ ታላቅ ይሆናል፥ ማንምም ወደ ሌላኛው ወገን ማለፍ አይችልም። የእኔ ቢሆኑም ባይሆኑም። የልብን መከፈል አሳይቼሻለሁ እናም ይመጣል። ልቦችን እከፍላለሁ ወደ እኔም የሚመጡትን አድናለሁምና። እንደ አምላካቸው የሚወዱኝ ሕዝቦች አሉኝ፥ ከእኔም ውጭ ሌላ ማንንም የማይወዱ።"*

"*መከፋፈሉ ሲጨምር ታላቅ ቀውስ ይጨምራል፥ ብዙዎች ራሳቸውን ለማዳንና ለደኅንነታቸው በማያሰጋ ቦታ ሲንቀሳቀሱ፥ ነገር ግን ብቸኛው (የደኅንነት) ቦታ የሚሆነው በቤቴ ውስጥ ነው። እውነትን ታውቃላችሁ፥ እናም በእርሱ ልትሄዱ ይገባል፥ እኔንም ለሚፈልጉ መንገዱን ማሳየት ይገባችኋል። የወዳደቀውን ትርፍራፊ ለማስተካከል ሳትሞክሩ የራሳችሁን ሩጫ ልትሮጡ ይገባችኋል፥ ነገር ግን ለእኔ ወደ መታዘዝ ጥሩአቸው፥ እናም እኔ ወደ እኔ የሚጮሁትን አስተካክላቸዋለሁ።"*

"*ይህ ከማጥራቱ ወቅት ጋር አንድ አይደለም። ይህ የትንሳኤና በምድር ከሚኖሩት ሕዝቤ የደረቁ አጥንቶች ወደ አብሮነት የሚመጡበት ነው። እኔ በአሜሪካ ብቻ አይደለም እየተንቀሳቀስሁ ያለሁት፥ በሁሉም ሀገራት እንጂ። የእኔ የሆኑት በሙላት (ሙሉ በሙሉ) ወደ እኔ የሚመጡበት አልያም በተቃራኒው ወገን የሚተዉበት ሰዓት መጥቷል። ልክ ሕዝቤን በሙሴ በኩል ወደ ተራራው ስጠራቸው እንደነበረው፥ የሰሙት፥ ወደ እኔ መጡ፥ ያልሰሙት ግን በታላቁ መንቀጥቀጥ ጠፉ፥ በድጋሚ እንዲሁ ይሆናል።"*

"*ከእንግዲህ ወዲያ በቤቴ ውስጥ ስርዓት አልበኝነትን አልታገስም። በእኔ ይሞቃል አልያም ያለ እኔ ይቀዘቅዛል። እኔ የሚባላ እሳት ነኝ፥ እናም ሕዝቤ ይቃጠላሉ በእኔም ይበላሉ፥ አልያም ባዶ መቃብሮች ይሆናሉ። የመገናኛውን ድንኳ አሳይቼሻለሁ። ድንኳኖቼን እንድታቀጣጥሉ ነግሬአችኋለሁ፥ ልክ አሁን ይህን የሚያደርጉ እንዳሉት፥ እንዳንቺ። ማቆም የለባችሁም። ያየሽው ማድጋ፥ የድንኳኖቼ በጋራ መነሣት ነውና። ተጀምሯል፥ ሕዝቤም እየተነሱ ነው።"*

"*ሂጂና ወደ ማድጋው ውስጥ ተመልከቺ"*

ወደ ማድጋው ሄድሁና ወደ ውስጥ ተመለከትሁ። በውኃ ተሞልቶ ነበር። ውኃ ይመስላል። እጄን ዘረጋሁና ውኃውን ነካሁት። ቀዝቃዛና የሚጋብዝ ነበር። ጌታ ከአጠገቤ ቆመና ራሱን ነቀነቀ። እንዲህ አለኝ፥ "*ውኃ አይደለም። በብርሃኔ ትቦዎች የሚመጣና በእሳቴ የሚነድዱትን ዋንጫዎች የሚሞላው ዘይት ነው። በህያው ዘይቴ እየሞላኋቸው ነው፥ እናም ራሴን በውስጣቸው፥ በእነርሱ በኩል፥ በእነርሱ ላይ እያቀጣጠልሁ ነው፥ ምክንያቱ ደግሞ ማንም ይህንን አደረግሁ እንዳይል። ይህ ማንም ሰው የሌለው፥ ሊኖረውም የማይችል ሰማያዊ እሳት ነውና። ቅዱስ ነው። እኔ ነኝ።"*

ከዚያም ጌታ በድጋሚ ወደ ውስጥ እንድመለከት ነገረኝ።

በድጋሚ ወደ ውስጥ ተመለከትሁኝ፥ እሳት ነበር። በዚህ ጊዜ ጌታ ፈገግ አለና ራሱ ወደ ውስጥ ዘረጋ፥ ጥቂትም ሰጠኝ። አለኝም፥ "*ይህ በመጨረሻው ሰዓት ለሕዝቤ የተዘጋጀው ታላቁ ድርሻ ነው። እስካሁን ተይዞ (ተገትቶ) ነበር፥ ቅዱስ ነውና፥ እናም ቅዱስ የሆነውን ነገር ከሁሉ ነገር አስበልጦ ለማያከብረው ትውልድ አልሰጠውም። የእኔ ቅድስና ታላቅ ዋጋ ያለው እንቁ ነው። ቃሌ እንደዛ እንቁ ሊታይና ሊከበር ይገባዋል። እኔ ህያው ቃልና ቅዱሱ እሳት ነኝ። ራሴንም ለማይወዱኝና ለማይፈልጉኝ አልሰጣቸውም።"*

ጌታ አሁንም እንድመለከት ነገረኝ።

እንደገናም ተመለከትሁ፥ እናም በዚህ ጊዜ፥ ታላቅ ማእበል በማድጋው ውስጥ ነበር። ተገርሜ ነበር። ከዚያም ጌታ እንዲህ አለ፥ “*ማእበሉ እየመጣ እንደሆነ ነግሬሻለሁ። በምድር ላይ የሆነና የሚመታ አይደለም። ማእበሉ የእኔ በሆኑትና ባልሆኑት መሀከል ሙሉ መከፋፈልን ያመጣል፥እናም የእኔን ፍትህ ያመጣል። ቅሬታዬ ራሷን አዘጋጅታለች እናም የእኔ ትንፋሽ ሙሉ በሙሉ ማስመለስን እስኪያመጣ እየጠበቀች ነው። ይህም ራሱ አሁን ጀምሯል። ወደ ስፍራቸው እያንቀሳቀስኳቸው ነው። ከምድር በላይ ሳልፍ፥ከእጄ በታች ይቆማሉ።*”

“*መቼ ይሆናል በሚለው አትጨነቂ፥ ነገር ግን በእነዚያ በሰጠሁሽ ነገሮች ተጨነቂ፥እናም ከፍ አድርጊያቸው፥ ልክ እንደነገርሁሽ። ምን ማድረግ እንዳለብሽ ታውቂያለሽ፥ የእኔ የቤት ሥራ የተሰጣቸው ሁሉ እንደሚያውቁት፥አሁን እንደዚያ የማድረጊያ ጊዜ ነው። ወደፊት ሰብሮ መሄጃው አሁን መጥቷልና እንዲሁም መከፋፈሉ። ከተቃውሞው የተነሳ ወደ ኋላ አትሰብሰቡ፥ነገር ግን በተልዕኮዬ ሩጡ፥እናም እኔ የራሴ የሆኑትን ስሰበስብ ተመልከቱ። መጋረጃው ሊገለጥ ሰዓቱ እየቀረበ ነው።*”

ጌታ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ማድጋው እንድመለከት ነገረኝ።

እንደዛው አደረግሁ፥ በዚህ ሰዓት ግን ፍርሀት ተሰማኝ። ጭንቅላቱን አነቃነቀ ስለዚህም ወደ ውስጥ ተመለከትሁኝ። በማድጋው ውስጥ ጥቁር ሞት ነበር። በመከፋት ራሱን አነቃነቀና እንዲህ አለኝ፥ “*አዎን። ጥቁሩ ሞት ይመጣል፥ ብዙዎችንም የራሱ ያደርጋል። አስጠንቅቄአለሁ ተጣርቻለሁ ጮኬማለሁ፥ እናም ጥቂቶች ብቻ ምላሽን ሰጥተውኛል፥አሁን እንኳን። ምን ሊሆን ነው፥አሁንስ ምን ይሆናል። ሞት ከማድጋው ይመጣል፥እቃዎቼ የምህረቴና የቁጣዬ መጠቀሚያዎች ናቸውና። የምነግራቸውን ሁሉ ይናገራሉ፥ፈቃዴንም ያደርጋሉ። ቃሌ ሰውን ሁሉ ይዳኛል። ሰዎች እንኳን እጣፈንታቸውን ይመርጣሉ። ቃሌ በእርግጥም ወደ ፊት ወጥቷል፥አሁን ልቦች ሁሉ ሲደነድኑ፥አሁንም ወደ ፊት እየወጣ ነው፥ብዙ መቅሰፍቶች ጀምረዋልና፥ነገር ግን ይጨምሩማሉና።*”

“*ልትሂጂና ልትተማመኚብኝ ይገባል። ፍፃሜሽን ካላሳካሽና አለመታዘዝን ከመረጥሽ፥ አንቺም ራስሽ ትጠፊያለሽ። የማይታዘዙኝ ሁሉ ይጠፋሉ። በዚህ ምድርም ይሁን ለዘላለም፥ለዘላለም ከእኔ ተለይተው። ማንም ነጻ አይደለም። አንቺ ራስሽ። ታውቂኛለሽ፥ ቃሎቼም በውስጥሽ ይኖራሉ፥ የእኔን መገኘትም (presence) ታውቂያለሽ፥ ከእሳቴም ተካፋይ ሆነሻል። ምንም ሰበብ የለሽም የግድ ልትከተዪኝ ይገባል። አታመንቺ፥ ነገር ግን ሂጂ፥ እኔ እንደገለጥሁልሽ ቃሌን ስጪ፥ አትፍሪም፥ እኔ ከአንቺ ጋር ነኝና፥ የእኔ ከሆኑት ከሁሉም ጋር ነኝ።*”

“*ንፋሳቱ እየነፈሱ ነው እናም መሰባበሩ ልዩነቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ይቀጥላል፥እንደተናገርሁት፥ስለዚህ ሂጂ፥ ሰዓቱ ረፍዷል፥ሕዝቡም ይጠብቁኛል። እኔ እረኛው ነኝና መንጋዎቼንም እሰበስባለሁ በጨለማውም መሀከል እረኛ እሆናቸዋለሁ በመካከሉም ስነሣ ክብሩ ታላቅ ይሆናል፥በምድር።*”

ከዚያም ጌታ ተለይቶኝ ሄደና እኔ በምድረ በዳው ውስጥ ቆሜ ቀረው።

ተፈፀመ።

-ሱዛን ከሚንግስ፥ አፕሪል 20፥2005 ዓ.ም ከምሽቱ 11፡44 (11፡44 PM)

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com